# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር

## በነዳጅ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የሚለወጡበትን አሠራር ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር …/2018

ጥቅምት 2018

አዲስ አበባ

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ከነዳጅ ተሽከርካሪዎች ትራንስፖርት ወደ ኤሌክትሪክ እና ታዳሽ ኃይል ትራንስፖርት ሽግግር ትግበራ መግባቷ ከትራንስፖርት ሴክተሩ ወደ አየር ንብረት የሚለቀቀውን የተቃጠለ ጋዝ  በመቀነስ ረገድ ቀዳሚ የሚያደርጋት ከመሆኑም ባሻገር ለአፍሪካ የኤሌክትሪክ እና ታዳሽ ኃይል ትራንስፖርት ስርፀትና አቅርቦት ትልቅ አንድምታ የሚኖረው በመሆኑ፤

መንግሥት በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚከሰቱ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስና ለመከላከል ከአየር ንብረት ጋር ተስማሚ የሆነ የትራንስፖርት ሥርዓት እንዲኖር በማቀድና በመተግበር ላይ ሲሆን በሁሉም ዘርፎች ፈጣን ዕድገት እያስመዘገበች ያለችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ዘላቂ የሆነና ምቹ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ለማስቻል ዘርፉን ከነዳጅ ጥገኝነት በማላቀቅ ወደ ኤሌክትሪክ እና ታዳሽ ኃይል ለማሸጋገር የሚደረገው ጥረት የሚበረታታ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ መንግሥት አሳሳቢ እየሆነ የመጣውን የአየር ብክለት ለመቀነስ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን አቅርቦትና ስርጭት ለመጨመር የሕግ ማዕቀፎችን በማውጣትና የግሉን ዘርፍ በመደገፍ ጉልህ የፖሊሲ እርምጃዎችን እየወሰደ ስለሆነ፤

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ “በነዳጅ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ሚለወጡበትን አሠራር ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር .../2018” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አግባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **“ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር”** ማለት የትራንፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒሰትር ማለት ነው፤
2) **“የብቃት ማረጋገጫ ሰጪ አካል”** ማለት ከውጭ ሀገር የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ለሚያስመጣ ወይም ለሚገጣጥም ወይም ለሚያመርት ድርጅት ወይም ግለሰብ ፈቃድ እንዲሰጥ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ትራንስፖርትን ለመምራትና ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የክልል መንግሥት አካል ነው፤
3) **ተሽከርካሪ ማለት** * ልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችን ሳይጨምር በመንገድ ላይ በመንኮራኩር የሚሄድ ማንኛውም አይነት ተሽከርካሪ ሆኖ ሰረገላን፣ሳይክልን፣ባለሞተር ተሽከርካሪን ግማሽ ተሳቢን እና ተሳቢን ያጠቃልላል
4) **ባለሞተር ተሽከርካሪ ማለት*** በመካኒካል ወይም በኤሌትሪካል ሀይል እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ሆኖ የጭነት ማመላላሻ ተሽከርካሪ፣ ባለሞተር ብስክሌት፣ የግል አውቶሞቢል፣ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ጎታች መኪና እና ልዩ ተንቀሳቃሽ መሳሪያን ያጠቃልላል፣
5) **“የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ”** ማለት በኤሌክትሪክ ኃይል አማካይነት የሚንቀሳቀስ የፍጥነት መጠኑ በሰዓት ከ20 ኪሎ ሜትር በላይ የሆነ በመንገድ ላይ በመንኮራኩር የሚሄድ ማንኛውም ዓይነት ተሽከርካሪ ነው፤
6) ”የሞተር ውስጥ ማቀጣጠያ” ማለት በሞተር ውስጥ ያለውን የኬሚካል ኢነርጂ ለኃይል ለማዋል ወደ ሜካኒካል ኃይል የሚቀይር የሞተር ተሽከርካሪ አካል ነው፤

7) **“በነዳጅ የሚሠራ ተሽከርካሪ”** ማለት ቤንዚን፣ ናፍጣ፣ ኬሮዚን እና የነዳጅ ዘይትን እንደ ኃይል ምንጭ አድርጎ የሚጠቀም ተሽከርካሪ ነው፤

8) **“ሞተር”** ማለት ኃይልን ወደ እንቅስቃሴ የሚቀይሩ ተንቀሳቃሽ ክፍሎች ያሉት ማሽን ነው፤

9) **“ተሽከርካሪን መቀየር”** ማለት በነዳጅ የሚሠራ ተሽከርካሪን የውስጥ ተቀጣጣይ ሞተርን በማደስ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ተሽከርካሪ የመለወጥ ሂደት ነው፤

10)**“ዋና የባትሪ መሙያ”** ማለት ዋና የኤሌክትሪክ አቅርቦትን በመጠቀም ባትሪን የሚሞላ መሣሪያ ነው፤

11)**“ዋና እሽግ ባትሪ”** ማለት የኤሌክትሪክ ኃይልን የሚያከማች እና ለኤሌክትሪክ ሥርዓት ኃይል የሚሰጥ መሣሪያ ሆኖ የሚፈለገውን የቮልቴጅ እና የአሁን ደረጃዎችን ለማግኘት በተከታታይ እና በትይዩ የተገናኙ ከበርካታ የባትሪ ሕዋሶች የተመሠረተ ነው፤

12) “**አጋዥ ባትሪ**” ማለት ለመብራቶች፣ ለአክሰሰሪዎች እና ለመልቲሚዲያ ሲስተም እና ለመሳሰሉት የተሽከርካሪ ኤሌክትሪክ አካላት ኃይል የሚሰጥ ሁለተኛ ደረጃ ባትሪ ነው፤

13) “**ጥቅል ማንቀሳቀሻ ባትሪ**” ማለት የተሽከርካሪውን ሞተር ለመጀመር እና የተለያዩ የኤሌክትሪክ ሥርዓ×ቶቹን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገውን የኤሌክትሪክ ኃይል ለማቅረብ የሚያስችል ባትሪ ነው፤

14) “**ማንቀሳቀሻ ባትሪ**” ማለት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪን፣ Plug-In-Hybrid ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪን ወይም Hybride ኤሌክትሪክን የሚያንቀሳቅስ ዳግም ሊሞላ የሚችል ባትሪ ሆኖ የተሽከርካሪውን ሞተር ለመጀመር እና የተለያዩ የኤሌክትሪክ ሥርአቶቹን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገውን የኤሌክትሪክ ኃይል ለማቅረብ የሚያስችል ነው፤

15) “**የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ባትሪ**” ማለት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ለማንቀሳቀስ የታመቀና ከፍተኛ የሀይል ጥግግት ያላቸው ዳግም ሊሞላ የሚችል የባትሪ ጥቅል ነው።

16) “**የሚቀየረው ተሽከርካሪ**” ማለት ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ለመለወጥ የተዘጋጀ ተሽከርካሪ

17) “**የኤሌክትሪክ ባትሪ መቆጣጠሪያ**” ማለት የባትሪውን አጠቃላይ ሁኔታ የሚቆጣጠር ኤሌክትሮኒካዊ ዑደት የሚከታተል የባትሪ ዓይነት ነው፤

18) “**የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ጋራዥ**” ማለት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ለመጠገን የሚያገለግል የሥራ ቦታ ነው፤

19) **“ኢንቨስትመንት ፈቃድ”** ማለት የወደፊት ገቢን ወይም ትርፍን ታሳቢ በማድረግ በአንድ ተቋም ወይም ድርጅት ላይ ገንዘቡን፤ ጉልበቱን እና እውቀቱን ማፍሰስ እንዲችል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

20) **“የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ”** ማለት ሞተራቸው በነዳጅ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎችን ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል ለሚቀይሩ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ከሚኒስቴሩ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

21) **“የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መሰረዝ”** ማለት ሞተራቸው በነዳጅ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎችን ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል በመቀየር ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ተደጋጋሚ ወይም ከባድ ጥፋት ሲያጠፉ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ ነው፤

22) **“የኃይል መሙያ መሠረተ ልማት”** ማለት በኤሌክትሪክ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን የኤሌክትሪክ ኃይል ለመሙላት የሚያገለግል መሠረተ-ልማት ነው፤

23) **“ተለዋዋጭ የኤሌክትሪክ ከረንት”** ማለት የሚቀያየር የኤሌክትሪክ ኃይል ፍሰት ነው፤

24) **“ቀጥተኛ የኤሌክትሪክ ከረንት”** ማለት የማይለዋወጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍሰት ነው፤

25) **“ተለዋዋጭ የኤሌክትሪክ ቻርጀር”** ማለት የሚቀያየር የኤሌክትሪክ ኃይል መሙያ ነው፤

26) **“ቀጥተኛ የኤሌክትሪክ ከረንት”** ማለት የማይለዋወጥ የኤሌክትሪክ ኃይል መሙያ ነው፤

27) **“ከፍተኛ ኃይል”** ማለት ማንኛውም የቮልቴጅ መጠኑ ከ 50 ቮልት ቀጥተኛ ወቅታዊ (30 ቮልት AC) በላይ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል ነው፤

28) **“ዲሲ ዲሲ ቻርጀር”** ማለት ከዋና የባትሪ መሙያ ላይ አጋዥ ባትሪን ለመሙላት የሚጠቅም ቻርጀር ነው፤

29) **“ማቀፊያ”** ማለት ኤሌክትሪክን ወይም የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችን እና የኤሌክትሪክ ንዝረትን የሚከላከል ካቢኔ ወይም ሳጥን ነው፤

30) **“ኤሌክትሪካል ቻሲስ”** ማለት በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ (ኢ.ቪ.) ውስጥ በኤሌክትሪክ ለሚገናኙ ክፍሎች የጋራ መሠረት ነው፤

31) **“መከላከያ”** ማለት በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ (ኢ.ቪ.) ውስጥ በኤሌክትሪክ ለሚገናኙ ክፍሎች የሚከላከል ክፍል ነው፤

32) **“ማፍጠኛ”** ማለት የፍጥነት መቆጣጠሪያ ፔዳል በሽቦ ወይም በሌላ መንገድ የሚሠራ ሆኖ ፖታንሺኦ ሜትር የሚንቀሳቀስበት ነው፤

33) **“የፍጥነት አመላካች”** ማለት የፍጥነት መቆጣጠሪያውን ፖታንሺኦ ሜትር የሚንቀሳቀስበትን ፔዳል አቀማመጥ በማንበብ ለሾፌሩ ምልክት የሚሰጥ መሣሪያ ነው፤

34) **“የፍጥነት መቆጣጠሪያ”** ማለት የኤሌክትሪክ ሞተሩን ዙር የሚቆጣጠር መሣሪያ ነው፤

35) "**የኃይል መቆጣጠሪያ**" ማለት ለደኅንነት እና ተግባራዊነት አስፈላጊ የሆነ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ቮልቴጅ የሚቆጣጠር መሣሪያ ነው፤

36) "**ኤሌክትሮ-ማግኔቲክ ተስማሚነት**" ማለት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ክፍሎች ከሌሎች የኤሌትሪክ እና የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ጋር ጣልቃ ሳይገባ እና በእነሱ ሳይነካ የመሥራት ችሎታ ነው፤

37)"**የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኃይል መሙያ ማሽን**" ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል መቀበያ ሶኬት ያለው ነው፤

38) "**ማገናኛ**" ማለት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪን እና የኤሌክትሪክ ኃይል መሙያ ማሽንን የሚያገናኝ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ነው፤

39) "**ደረጃ**" ማለት በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት በቁጥር ES7073:2024 የወጣው ስታንዳርድ ነው፤

40) "**ቀያሪ ድርጅት**" ማለት አግባብነት ባለው የንግድ ሕግ መሠረት ተመዝግቦ ሞተራቸው በነዳጅ የሚሠራ ተሽከርካሪዎችን ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል የመቀየር አገልግሎት ለመስጠት በዚህ መመሪያ መሠረት ከሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ አካል ነው፤

41) "**ሰው**" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

42) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በተመዘገቡ በማንኛውም ከነዳጅ ተሽከርካሪነት ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪነት በሚቀየሩ ተሽከርካሪዎች ላይ፣ በተሽከርካሪዎቹ ባለንብረቶች ላይ እና በቀያሪ ድርጅቶች እና ጋራዦች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. <u>ዓላማ</u>

በነዳጅ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ለመቀየር የወጣውን ደረጃ መሠረት በማድረግ በአገር-አቀፍ ደረጃ በወጥነት ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ ተሽከርካሪዎቹ ሲቀየሩ ደኅንነታቸው የተረጋገጠ፣ ለአካባቢ ተስማሚ እና ምቹ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 5. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

1) ከነዳጅ ተሽከርካሪ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የመቀየር አገልግሎት ለሚሰጡ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤
2) ከነዳጅ ተሽከርካሪ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የመቀየር አገልግሎትን የሚመለከቱ የአሠራር ማንዋሎችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤
3) ከነዳጅ ተሽከርካሪ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የመቀየር አገልግሎት ለሚሰጡ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች የአገልግሎት ክፍያ ይወስናል፤
4) ከነዳጅ ተሽከርካሪ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የመቀየር አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጠጥ እና ተያያዥ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እና ከክልሎች ጋር የሥራ ግንኙነትን በማጠናከር ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
5) ከነዳጅ ተሽከርካሪ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ በመቀየር **አገልግሎት** ዙሪያ በሚካሄዱ ሀገር-አቀፍ፣ አህጉር-አቀፍ እና ዓለም-አቀፍ ዓውደ ጥናቶች፤ ወርክ ሾፖች፣ ሴሚናሮች፣ ሲምፖዚየሞች ላይ ይሳተፋል፤ ያዘጋጃል፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን ያስፋፋል፤
6) ከነዳጅ ተሽከርካሪ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ለመቀየር በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የወጣው ደረጃ እንዲሻሻል ያደርጋል፣ ሲወጣም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
7) ከነዳጅ ተሽከርካሪ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የመቀየር አገልግሎት ስፔሲፊኬሽን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
8) ለተበላሸ ወይም ለጠፋ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሕጋዊ ማስረጃ ሲቀርብ ምትክ ይሰጣል፤
9) የመመሪያውን ተግባራዊነት ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣተራል፤
10) መመሪያውን ተላልፈው በሚገኙ አካላት ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል።

### 6. በነዳጅ የሚሠራ ተሽከርካሪን ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የሚቀይሩ ድርጅት ግዴታዎች

ከነዳጅ የሚሠራ ተሽከርካሪን ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የሚቀይር ማንኛውም ድርጅት የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

1) ከሚኒስቴሩ የቀያሪነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የመውሰድ፤
2) ለሚቀይራቸው ተሽከርካሪዎች የመለዋወጫ ዕቃ የማቅረብ፤
3) ለቀየራቸው ተሽከርካሪዎች የጥገና አገልግሎት የመስጠት፤
4) የሚቀይራቸው ተሽከርካሪዎች ሀገሪቱ ባወጣችው ደረጃ መሠረት መሆናቸውን የማረጋገጥ፤
5) የሚቀይራቸው ተሽከርካሪዎች ላይ የሚገጠሙ ዕቃዎችን የምርት ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማቅረብ፤
6) ለሚቀይራቸው ተሽከርካሪዎች ቢያንስ አራት የዲሲ የቻርጅ ማድረጊያ ማሽን የማዘጋጀት፤
7) የቀየራቸውን ተሽከርካሪዎች መረጃ በዓይነትና በቁጥር በመመዝገብ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት የማድረግ፤
8) የጥገና አገልግሎት መስጫ ማዕከል /ጋራዥ/ የማደራጀት፤
9) ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በየዓመቱ የማሳደስ፤
10)ለሚቀይራቸው ተሽከርካሪዎች እና ለባትሪያቸው ቢያንስ የስድስት ዓመት ዋስትና የመስጠት፤
11)የሚቀይራቸው ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የቴክኒክ ብቃት ምርመራ ማረጋገጫ ያቀረቡ መሆኑን የማረጋገጥ፤
12)ለሚቀይራቸው ተሽከርካሪዎች የትውውቅ እና የድኅረ-አገልግሎት ሥልጠና የመስጠት
13)ተጨማሪ የአገልግሎት መስጫ ቅርንጫፍ ሲከፍት ለሚኒስቴሩ የማሳወቅና ፈቃድ የመውሰድ፤
14) ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው መስፈርት መሠረት የመስሪያ ቦታ፣ የሰው ኃይል እና የሥራ እና የሥራ ላይ ደኅንነት መሣሪያ የማሟላት፤
15)የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ለሌላ 3ኛ ወገን አሳልፎ ያመስጠት፤
16)የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የማመልከቻ ፎርሙን ሞልቶ ካስገባበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ የሥራ ቦታውን እና የሥራ መሣሪያዎችን በሚኒስቴሩ የማስገምገም፤

## 7. <u>የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች</u>

ከነዳጅ የሚሠራ ተሽከርካሪን ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የሚቀይር ማንኛውም ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡-

1) የድርጅቱ ባለቤት ወይም ስራ አስኪያጅ ስም እስከ አያትና አድራሻ፣ ከተማ፣ ክልል፣ ዞን፣ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የስልክ ቁጥር፣ በአመልካቹ የተሞላ እና የተፈረመ ማመልከቻ ቅጽ፣
2) አመልካቹ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተነሳው 2 ጉርድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶ ግራፍ፣
3) የአመልካቹን ማንነት የሚገልፅ ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ፣ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም የጸና የፓስፖርት ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ፣
4) ጥያቄው የቀረበው በወኪል አማካይነት ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተጠቀሱት ሰነዶች በተጨማሪ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ፤
5) ሕጋዊ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/በኪይ ከሆነ ሕጋዊ የኪራይ ውል ማስረጃ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ፣
6) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ፣
7) ከዚህ መመሪያ በተያያዘው ሠንጠረዥ የተቀመጠውን የሰው ኃይል፣ የትምህርት ማስረጃ እና ሕጋዊ የቅጥር ውል ማስረጃ፣

## 8. <u>ቀያሪ ድርጅቶች/ጋራዦች/ ለባለንብረቶች ያሉባቸው ግዴታዎች</u>

ከነዳጅ ተሽከርካሪ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የሚቀይሩ የጋራዥ ድርጅቶች የተቀየሩ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ትክክለኛ አያያዝ እና አጠቃቀም ለመረዳት የሚያስችሉ የሚከተሉትን ሰነዶች አዘጋጅተው ለተሽከርካሪ ባለቤቶች አዘጋጅቶ ማቅረብ አለባቸው፡-

1) ከነዳጅ ተሽከርካሪ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ አለዋወጥን የሚገልጹ ሰነዶች አዘጋጅቶ የማቅረብ፤
2) ተሽከርካሪው ሲቀየር የተጨመሩ መሣሪያዎች እና ክፍሎች ዝርዝሮች የማቅረብ፤
3) የመመርመሪያ፣ የጥገና፣ የአካል ክፍሎችን እና የባትሪ መተካት ሂደቶችን ጥገና የሚገልጹ የአሠራር ሂደቶችን ማንዋሎችን ዘአጋጅቶ የማቅረብ፤
4) አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ዝርጋታ ንድፎች አዘጋጅቶ የማቅረብ፤

5) የተቀየሩ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን አጠቃቀም ጥገና እና አስተዳደር ሙሉ ለሙሉ ለተጠቃሚዎች የማስረዳት፤

6) የተሽከርካሪ ቀያሪ ድርጅቶች/ግለሰቦች ስለ ቻርጅ መሙያ መሣሪያዎች እና የኃይል መሙያ ዘዴዎች ሙሉ መረጃ ለተጠቃሚዎች የማስረዳት፤

7) የተቀየረውን ተሽከርካሪውን የምርት ማሻሻያ ዘመን የሚገልፅ ሕጋዊ ሰነድ ማቅርብ፤

8) የሚቀየረውን ተሽከርካሪው የምርት ማሻሻያ መለያ ቁጥር የሚገልፅ ሕጋዊ ሰነድ የማቅረብ፤

9) የሚቀየረውን የተሽከርካሪ የምርት ማሻሻያ በማን እንደተሻሻለ የሚገልፅ ሕጋዊ ሰነድ የማቅርብ፤

10)የሚቀየረውን የተሽከርካሪ ኤሌትሪካል ሞተሮች መለያ ቁጥር የሚገልፅ ሕጋዊ ሰነድ የማቅርብ፣

11)የሚቀየረውን የተሽከርካሪ የባትሪ አቅም የሚገልፅ ሕጋዊ ሰነድ የማቅረብ፣

12)የሚቀየረውን የተሽከርካሪው አጠቃላይ ክብደት የሚገልፅ ሕጋዊ ሰነድ የማቅረብ፤

13)የሚቀየረውን የተሽከርካሪው ነጠላ ክብደት የሚገልፅ ሕጋዊ ሰነድ የማቅረብ፤

14) የሚቀየረውን የተሽከርካሪው የመጫን አቅም የሚገልፅ ሕጋዊ ሰነድ የማቅረብ፤

15)የሚቀየሩት ተሽከርካሪዎች እድሜ ለህዝብ ትራንስፖርት 20 ዓመት ያልበለጠ ሆኖ መደበኛ **የመሪ ሲስተም፣የፍሬን ሲስተም፣ቦዲ እድሳት** ሊደረግለት ይገባል፤

## 9. <u>ከነዳጅ ተሽከርካሪ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የሚቀይር ባለንብረት ግዴታዎች</u>

1) ከነዳጅ ወደ ኤሌትሪክ ተሽከርካሪ እንዲቀየርለት ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ሰነዶች ማሟላት አለበት፦

ሀ) የተሽከርካሪ የባለቤትነት ደብተር/ሊብሬ/፤

ለ) በመዝጋቢ ተቋማትኮንፒውተር የተመዘገበ ዕዳና ዕገዳ የሌለበት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ሰነድ፤

ሐ) የዘመኑን ግብር የከፈለ መሆኑን የመገልጽ የግብር ክሊራንስ፤

መ) ከቀረጥ ነፃ የገባ ተሽከርካሪ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተጻፈ የፈቃድ ደብዳቤ፤

ሠ) የተሽከርካሪው እድሜ ለአውቶሞቢል እና ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ከ20-25 ዓመት በታች የሆነ እንደ ቅደም ተከተላቸው፤

ረ) አጠቃላይ ክብደቱ ከ3500 ኪ.ግ በታች የሆነ መሆኑን ማረጋገጥ፤

2) ተሽከርካሪውን ሕጋዊ እና የታደሰ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ባለው ድርጅት /ጋራዥ/ ብቻ የማስቀየር፤

3) ተሽከርካሪውን በተቀመጠው የተሽከርካሪ ዕድሳት ደረጃ መሠረት ብቻ የማስቀየር፤

4) የተቀየረውን ተሽከርካሪ ለማስመዝገብ ወደ መዝጋቢ አካል ሲሄድ የቀያሪው ድርጅት ማኅተም ያረፈባቸውን የሚከተሉትን ሰነዶች ለተሽከርካሪ መዝጋቢ አካል የማቅረብ፡-

ሀ) የተቀየረውን ተሽከርካሪውን የምርት ማሻሻያ ዘመን የሚገልፅ ሰነድ፤

ለ) የተቀየረውን የተሽከርካሪ የምርት ማሻሻያ መለያ ቁጥር የሚገልፅ ሰነድ፤

ሐ) የተቀየረውን ተሽከርካሪ የምርት ማሻሻያ በማን እንደተሻሻለ የሚገልፅ ሰነድ፣

መ) የተቀየረውን ተሽከርካሪ የኤሌትሪካል ሞተሮች መለያ ቁጥር የሚገልፅ ሰነድ፣

ሠ) የተቀየረውን ተሽከርካሪ የባትሪ አቅም የሚገልፅ ሰነድ፣

ረ) የተቀየረውን ተሽከርካሪ አጠቃላይ ክብደት የሚገልፅ ሰነድ፣

ሰ) የተቀየረውን ተሽከርካሪ ነጠላ ክብደት የሚገልፅ ሰነድ፣

ሸ) የተቀየረውን ተሽከርካሪ የመጫን አቅም የሚገልፅ ሰነድ፣

ቀ) የተቀየረውን ተሽከርካሪ ዓመታዊ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት፣

በ) ከባለ ጋራዥ ጋር የተዋዋለውን ውል ሰነድ እና የባለጋራዡን የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ፣

# ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 10. ክልከላዎች

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ መመዘኛ መስፈርት ሳያሟላ ማንኛውም አካል ከነዳጅ ተሽከርካሪ ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ መቀየርም ሆነ ማንኛውንም የኤሌክትሪክ ባህሪ ወደ አለው ተሽከርካሪነት መቀየር የተከለከለ ነው፡፡

### 11. አስተዳደራዊ ቅጣት

በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ አካል ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 7 ላይ የተመለከተው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

### 12.የመተባበር ግዴታ

ይህ መመሪያ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም አካል አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት

### 13. የቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት

1) በመመሪያው መሠረት በተሰጠው አገልግሎት ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል ቅሬታውን አገልግሎቱን ለሰጠው አካል ኃላፊ ቅሬታው በተፈጠረ በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

2) ኃላፊው ለቀረበው ቅሬታ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

3) ኃላፊው በሰጠው ምላሽ ቅር የተሰኘ ሰው ቅሬታውን በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለሚኒስትሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

4) ሚኒስትሩ ለቀረበው ቅሬታ በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል።

5) ሚኒስቴሩ የሚሰጠው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡

### 14. አባሪ ሰነዶች

በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የወጣው ደረጃ፣ ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዙት ሌሎች አባሪዎች እና ቅፆች የዚህ መመሪያ አካል ይሆናሉ፡፡

## 15. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

*የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ልማዳዊ አሠራርና የአሠራር ሥርዓት በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡*

## 16. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 17. <u>መመሪው ሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከ ......ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር)**

**የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር**

# አባሪዎች

1. ለቀላል የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ጋራዥ የሰው ሀይል መስፈርት

| ሀ. | የሰው ሀይል አደረጃጀት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | ዝቅተኛተፈላጊ የትምህርት ዝግጅት | ብዛት | የስራ ልምድ | ምርመራ |
| 1. | ሥራ አስኪያጅ | በማኔጅመንት፣ በመካኒካል፣ ኤሌክትሪክ እና በሌሎች ተዛማጅ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለዉ/ያላት | 1 | 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ በአመራርነት የሰራ/የሰራች | |
| 2. | የተሽከርካሪ ኢንስፔክተር | በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች እና ከዚያ በላይ አውቶሞቲቭ ኤሌትሪካል እና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 1 | 5 ዓመት ለዲፕሎማ 8 ዓመት ለ10+3 እና 3 ዓመት ለዲግሪእና ከዚያ በላይ እና ከዚያ በላይ | |
| 3. | የንብረት ክፍል ሠራተኛ | በማንኛዉም የትምህርት መስክ በዲፕሎማ/10+3 የሰለጠነ በደረጃው COC የወሰደ/ች | 1 | 2/4ዓመት እና ከዚያበላይ | |
| 4. | ፎርማን | ሜካኒካል፣ማኑፋክቸሪንግ፣ አዉቶሞቲቭ፣ ኤሌትሪካል እና በተመሳሳይ የትምህርት | 1 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መስክ በዲፕሎማ/10+3 COC የወሰደ/ች ከዚያ በላይ የሰለጠነ/ች | | | |
| 5. | መካኒክ | በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች እና ከዚያ በላይ አውቶሞቲቭ ኤሌትሪካል እና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 2 | 3/5/1ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 6. | Electrical Engineer ኤሌክትሪካል ኢንጂነር | በዲግሪ እና ከዚያ በላይ Authomotive or Electrical Engineering or Mechatronics Engineering. Specialized training in EV power systems የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 2 | 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 7. | ረዳት ኤሌክትሪሽያን | 10+2/ በደረጃው COC፣ ዲፕሎማ እና ከዚያ በላይ የወሰደ/ች ኤሌክትሪካል፤ አዉቶሞቲቭ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 2 | 2/1/0 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 8. | ረዳት መካኒካል ኢንጂነር /Assistance Mechanical Engineer/ | በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች ሜካኒካል፤ አዉቶሞቲቭ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ | 2 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 9. | Battery Specialist / Technician/ | በዲፕሎማ/በዲግሪ በደረጃው COC የወሰደ/ች በElectrical | 1 | 4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | Engineering, Battery Technology, or EV-specific certification የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | | | |
| 10. | Software Engineer / Technician | በዲግሪ በSoftware Engineering, Computer Science, or Electronics አውቶሞቲቩን መሰረት ባደረገ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 1 | 0 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 11. | Safety and Compliance Officer | ሰርተፍኬት in automotive safety standards, ዲግሪ በኢንጅነሪንግ with additional coursework in EV safety. | 1 | 0 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 12. | **Safety Officer** | ፐብሊክ ሄልዝ ዲግሪ | 1 | 1 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 13. | የተሽከርካሪ አካል ሰራተኛ/ | ከ10ኛ ክፍል በላይ | 2 | 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ በተሽከርካሪ አካል ስራ | Body Painters and Finishers/ |

**ሠንጠረዥ 2፡-የኤሌክትሪክ የሞተር ሳይክል (ባለ2፣ ባለ3 እና ባለ4) እግር ጋራዥ የሰው ሀይል መስፈርት**

| ሀ. | የሰው ሀይል አደረጃጀት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | ዝቅተኛተፈላጊ የትምህርት ዝግጅት | ብዛት | የስራልምድ | ምርመራ |
| 1. | ሥራ አስኪያጅ | በማኔጅመንት፣ በመካኒካል፣ ኤሌክትሪክ እና በሌሎች ተዛማጅ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለዉ/ያላት | 1 | 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ በአመራርነት የሰራ/የሰራች | |
| 2. | የተሽከርካሪ ኢንስፔክተር | በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች እና ከዚያ በላይ አውቶሞቲቭ□ ኤሌትሪካል እና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 1 | 5 ዓመት ለዲፕሎማ 8 ዓመት ለ10+3 እና 3 ዓመት ለዲግሪእና ከዚያ በላይ እና ከዚያ በላይ | |
| 3. | የንብረት ክፍል ሠራተኛ | በማንኛዉም የትምህርት መስክ ከቴክኒክ እና ተመሳሳይ ሙያ የሰለጠነ በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች | 1 | 2/4ዓመትእናከ ዚያበላይ | |
| 4. | ፎርማን | ሜካኒካል፤ማኑፋክቸሪንግ፤ አዉቶሞቲቭ፣ ኤሌትሪካል | 1 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | እና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ በዲፕሎማ/10+3 COC የወሰደ/ች ከዚያ በላይ የሰለጠነ/ች | | | |
| 5. | የጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያ | በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች አውቶሞቲቭ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 1 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 6. | መካኒካል ኢንጂነር /Automotive Mechanical Engineer/ | በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች ሜካኒካል፤ አዉቶሞቲቭ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ | 1 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 7. | Electrical Engineer ኤሌክትሪካል ኢንጂነር | በዲግሪበElectrical Engineering or Mechatronics,Engineering. Specialized training in EV power systems የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 1 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 8. | ረዳት ኤሌክትሪሽያን | 10+2/10+1 በደረጃው COC የወሰደ/ች አዉቶኤሌክትሪካል፤ አዉቶሞቲቭ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 4 | 1/2ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 9. | ረዳት መካኒካል ኢንጂነር /Assistance | በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች ሜካኒካል፤ | 3 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | Mechanical Engineer/ | አዉቶሞቲብ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ | | | |
| 10. | Battery Specialist / Technician | በዲፕሎማ/በዲግሪ በደረጃው COC የወሰደ/ች በElectrical Engineering, Battery Technology, or EV-specific certification የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 1 | 1 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 11. | Software Engineer / Technician | በዲግሪ በSoftware Engineering, Computer Science, or Electronicsአውቶሞቲቩን መሰረት ባደረገ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 2 | 1 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 12. | Safety Officer | ፐብሊክ ሄልዝ ዲግሪ | 1 | 1 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 13. | የተሽከርካሪ አካል ሰራተኛ/ | ከ10ኛ ክፍል በላይ | 2 | 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ በተሽከርካሪ አካል ስራ | |

**ሠንጠረዥ 3፡- ለመካከለኛ እና ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ጋራዥ የሰው ኃይል መስፈርት**

| ሀ. | የሰው ሀይል አደረጃጀት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | ዝቅተኛተፈላጊ የትምህርት ዝግጅት | ብዛት | የስራልምድ | ምርመራ |
| 1. | ሥራ አስኪያጅ | በኤሌክትሪክ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለዉ/ያላት | 1 | 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 2. | የተሽከርካሪ ኢንስፔክተር | በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች አውቶሞቲቭ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 1 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 3. | የንብረት ክፍል ሠራተኛ | በማንኛዉም የትምህርት መስክ ከቴክኒክ እና ተመሳሳይ ሙያ የሰለጠነ በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች | 1 | 2/4ዓመትእናከ ዚያበላይ | |
| 4. | ፎርማን | ሜካኒካል፤ማኑፋክቸሪንግ፤ አዉቶሞቲቭ፣ ኤሌትሪካል እና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ በዲፕሎማ/10+3 COC የወሰደ/ች ከዚያ በላይ የሰለጠነ/ች | 1 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5. | የጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያ | በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች አውቶሞቲቭ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 1 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 6. | መካኒክ /Mechanical Engineer/ | በዲፕሎማ/10+3በደረጃው COC የወሰደ/ች ሜካኒካል፤ አዉቶሞቲቭ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ | 1 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 7. | Electrical Engineer ኤሌክትሪካል ኢንጂነር | በዲግሪ በElectrical Engineering or Mechatronics Engineering. Specialized training in EV power systems የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 2 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 8. | ረዳት ኤሌክትሪሽያን | 10+2/10+1 በደረጃው COC የወሰደ/ች አዉቶኤሌክትሪካል፤ አዉቶሞቲቭ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 4 | 1/2ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 9. | ረዳት መካኒካል ኢንጂነር /Assistance Mechanical Engineer/ | በዲፕሎማ/10+3 በደረጃው COC የወሰደ/ች ሜካኒካል፤ አዉቶሞቲቭ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የሰለጠነ | 3 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 10. | Battery Specialist / Technician | በዲፕሎማ/በዲግሪ በደረጃው COC የወሰደ/ች | 2 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በElectrical Engineering,Battery Technology, or EV-specific certification የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | | | |
| 11. | **Software Engineer / Technician** | በዲግሪ በSoftware Engineering, Computer Science, or Electronicsአውቶሞቲቭን መሰረት ባደረገ የትምህርት መስክ የሰለጠነ/ች | 2 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 12. | **Safety and Compliance Officer** | ሰርተፍኬት in automotive safety standards, ዲግሪ በኢንጅነሪንግ with additional coursework in EV safety | 2 | 2/4 ዓመት እና ከዚያ በላይ | |
| 13. | የተሽከርካሪ አካል ሰራተኛ/ | ከ10ኛ ክፍል በላይ | 2 | 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ በተሽከርካሪ አካል ስራ | |

**ሠንጠረዥ 4:- <u>ሞተራቸው በነዳጅ የሚሰሩትን መካከለኛ እና ከፍተኛ ተሽከርካሪዎችን ወደ ኤሌትርክ ሀይል የሚቀይሩ ጋራዥ ወርክሾፕ አደረጃጀት መስፈርት</u>**

| Workshop tool and equipment | | Specification |
|---|---|---|
| 1 | Air compressor | 125psi |
| 2 | Electric Power generator | 1generator with 20KVA |
| 3 | Tools | 6 set |
| 4 | Lifting devises | >15 tone |
| 7 | High Voltage Tester CAT IV 1000V. | 1 |
| 8 | High Voltage Insulation Tester CAT III. | 1 |
| 9 | Insulated Safety Clamp 1000V | 1 |
| 10 | Extra Long Insulated Hex Key Set | 1 Set |
| 11 | Insulated Tool Kit 3/8″D | 1 Set |
| 12 | Insulated Magnetic Pick Up Tool. | 1 |
| 13 | 1000V Insulated Inspection Mirror 50mm. | 1 |
| 14 | Test Probe Kit — Slim Fit. | 1 |
| 15 | AA/C diagnostics and recharging station | 1 |
| 16 | AC (alternating current)or DC fast charging station<br>(direct current) charging station | 1 |
| 17 | Training center | 1 |
| 18 | Break and suspension testing machine | 1 |
| 20 | Personal protection kit (poles, glove, Electrician's Insulating Rubber Safety Mat 1 x 1m,Exclusion Zone Extension Kit, ,High Voltage Warning Sign | 2 |

| | | |
|---|---|---|
| 21 | የደረቅና  ፈሳሾች ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ | 1 |
| 22 | እሳት ማጥፊያ | 3 pic |
| 23 | የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጪያ | 3 pic |

| ሀ. | **ሞተራቸው በነዳጅ የሚሰሩትን ሞተር ሳይክል፣ ባለሶስት እና ባለአራት እግር ወደ ኤሌክትሪክ ሀይል የሚቀይሩ ጋራዥእና ግለሰብ  ወርክሾፕ አደረጃጀት መስፈርት** | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **Workshop tool and equipment** | | **Specification** | | | |
| 1 | Electrical Air compressor | 90psi(6Bar | | | |
| 2 | Electric Power Generator | 1 generator with 10KVA | | | |
| 3 | Tools | 2 Set | | | |
| 4 | Lifting devises | 1 devises(>10 tone | | | EV battery lift, lifting capacity (lifting capacity: 1000kg, min. height 570mm, max. height 1780mm |
| 6 | Break and suspension test machine (for three wheelers) | 1 test machine | | | Break and suspension |
| 7 | Voltage Tester | 1 | | | |
| 8 | Oscilloscope 4425A oscilloscope | 1 | | | |
| 9 | AA/C diagnostics and recharging stations | 1 | | | |
| 11 | AC (alternating current)or DC fast charging stations<br>(direct current) charging stations | 1 | | | |
| 12 | Training center | 1 | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 13 | Insulated Tools | 1 | | | |
| 14 | Personal protection kit (poles, glove, Electrician's Insulating Rubber Safety Mat 1 x 1m,Exclusion Zone Extension Kit, ,High Voltage Warning Sign | 1 | | | |
| 15 | የደረቅና ፈሳሾች ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ | 1 | | | |
| 16 | እሳት ማጥፊያ | 3 pic | | | |
| 17 | የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጪያ | 3 pic | | | |

ሠንጠረዥ 5፡-**<u>የኤሌክትሪክ የሞተር ሳይክል (ባለ2፣ ባለ3 እና ባለ4) እግር ጋራዥ የስራ ቦታ መስፈርት</u>**

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | የቦታ ስፋት በካ.ሜ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የቀላል ተሽከርካሪ | የመካከለኛ ና የከባድ ተሽከርካሪ |
| | | ባለ 2 እግር | ባለ 3 እግር | ባለ 4 እግር | | |
| 1 | የሥራ አስኪያጅ/ እና ቢሮ፣ | 12 | 12 | 12 | 12 | 12 |
| 2 | የፀሐፊ እና የእንግዳ መቀበያ ቢሮ | 12 | 12 | 12 | 12 | 12 |
| 4 | የምርት/የመገጣጠሚያ ክፍል | 70 | 90 | 120 | 150 | 250 |
| 5 | የሥልጠና ክፍል | 20 | 25 | 30 | 30 | 30 |
| 6 | መታጠቢያና መጸዳጃ ቤት | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 8 | የኤሌክትሪክ ቻርጅ ማድረጊያ ቦታ | 10 | 15 | 20 | 50 | 90 |
| 9 | የሚገጣጠሙ እቃዎችን ማስቀመጫ (ስቶር) | 30 | 40 | 40 | 70 | 80 |
| 10 | ተሽከርካሪ ሰርቪስ ማድረጊያ ቦታ | 20 | 40 | 60 | 90 | 100 |
| 11 | ግቢው ቢያንስ ጠጠር የለበሰ መሆን አለበት | | | | | |
| 12 | መገጣጠሚያ ግቢው ቢያንስ በሽቦ የታጠረ መሆን ይኖርበታል | | | | | |
| 13 | የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ ያለው | 6 | 6 | 6 | 6 | 6 |
| | **ጠቅላላ ስፋት** | **190** | **250** | **310** | 430 | 590 |

## ሠንጠረዥ 7፡- የእርምጃ አወሳሰድ ሥነ-ሥርዓት እና የቅጣት እርከን

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነት | የመጀመሪያ ደረጃ እርምጃ | የሁለተኛ ደረጃ እርምጃ | ሦስተኛ ደረጃ እርምጃ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በወቅቱ አለማሳደስ | መታደስ ከነበረበት 1 ወር ካለፈው የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዳቸውን እንዲያሳድሱ በደብዳቤ ማሳወቅ | መታደስ ከነበረበት 3 ወር ካለፈው ለ3 ወር ከአገልግሎት ማገድ | መታደስ ከነበረበት ከ6 ወር በላይ ከሆነው የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መሰረዝ |
| 3 | በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ያጓደለ | የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት አገልግሎት እየተሰጠው በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ አስተካክሎ ሪፖርት እንዲያደርግ በጽሑፍ ማሳወቅ | ለ6 ወር የዕድሳት አገልግሎት እንዳያገኝ ማድረግ | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ለ1ዓመት ዓመት ማገድ |
| 4 | ወደ ኤክትሪክ የቀየራቸውን ተሽከርካሪዎች መረጃ በወቅቱ ሪፖርት ያለማድረግ | የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት አገልግሎት እየተሰጣቸው በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ አስተካክለው ሪፖርት እንዲያደርጉ በጽሑፍ ማሳወቅ ፣ | የዕድሳት አገልግሎት እንዳያገኝ ማድረግ | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዳቸውን ለሁለት ዓመት ማገድ |
| 5 | በሚመለከተው አካል ተፈላጊውን መረጃ ሲጠየቅ አለመስጠት | የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት | ለ3 ወር ከአገልግሎት ማገድ | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለ6ወር ማገድ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6 | የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድን ለሌላ ወገን አሳልፎ መስጠት | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለ6ወር ማገድ | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለ2 ዓመት ማገድ | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መሰረዝ |